ተፈፀመ/"It is Finished"/ τετέλεσται

— ዮሐንስ 19፥30 (አዲሱ መ.ት) ። "ኢየሱስም ሆምጣውን ከተቀበለ በኋላ፣ "<u>ተፈጸመ</u>" አለ፤ ራሱን አዘንብሎ፣ መንፈሱን አሳልፎ ሰጠ።"

— "<u>ተፈጸመ</u>" በሚለው ቃል ላይ ተመስርተን በዋናነት ሶስት ነገሮችን እንመለከታለን ። 1ኛ, ተፈፀመ የሚለው ቃል ለቀድሞ ዘመን ሰዎች የሚሰጠው ትርጉም ፣ 2ኛ, ተፈፀመ የሚለው ቃል ስነ መለኮታዊው ፋይዳው እና 3ኛ, በመስቀል ላይ የተፈፀመው ስራ ለእኛ ያስገኘው ውጤት ።

"ተፈጸመ" የሚለው ቃል ከሶስቱ ወንጌላት በተለየ ሁኔታ ዮሐንስ ሲጠቀመው እንመለከታለን ። ዮሐንስ 19፡30 ። ኢየሱስ በመስቀል ላይ የተናገረው የመጨረሻ ቃል ነው ። ተፈፀመ የሚለው የግሪክ ቃል **τετέλεσται** የሚል ሲሆን ይህ የግሪክ ግሥ perfect tense, passive voice, and indicative mood. ነው ። ይህ ግስ የሚያመለክተው ድርጊቱ ሙሉ በሙሉ መጠናቀቁን እና ውጤቱም እስከ አሁን ድረስ እንደሚቀጥል ነው ።

ይህ ግስ በ 1st-century በ Greco-Romanን አለም እንዴት ነበር ሲጠቀሙት የነበረው ?

በተለያየ አቅጣጫ ይህንን ቃል ቢጠቀሙም ለተመሳሳይ አለማ ነው ቃሉን የሚያውሉት ። ለምሳሌ :- 1, ለ Business ይህንን ቃል ይጠቀሙት ነበር ።"Paid in Full". በእዚያን ዘመን ግብይት ሲያካሂዱ በደረሰኝ ወይም በተለያየ የውል ማስረጃዎች ላይ ላይ ሊሆን ይችላል የግብይት ስርአቱ ሙሉ በሙሉ ሲፈፀም ማህተም የተደረገበት "ሙሉ በሙሉ የተከፈለ" የሚለውን ለመግለጽ **τετέλεσται** የሚለውን ቃል ይጠቀማሉ ።

2, Military: አንድ ወታደር ጦርነት ሲያሸንፍ **τετέλεσται** ብሎ ሊጮህ ይችላል። 3, Servants and Artists: "It's done. It's perfect. የሚለውን ሃሳብ ለመግለጽ **τετέλεσται** የሚለውን ቃል ይጠቀማል ። አንድ አገልጋይ አንድን ተግባር ሲያጠናቅቅ ወይም አርቲስት አንድን ሥራ ሲጨርስ **τετέλεσται** "ተከናውኗል. ፍጹም ነው" ይላሉ ። ኢየሱስም በሞቱ ጊዜም ቢሆን ተፈፀመ ሲል የሸንፈት ጩኸት አይደለም ያሰማው ፣ የድል መግለጫ ነው ያሰማው ። ኢየሱስ ይህንን ቃል ሲጠቀም "The work is complete. The victory is won. The debt is paid." እያለ ነው ።

ተፈፀመ የሚለው ቃል ስነመለኮታዊ ፋይዳው

1ኛ, Old Covenant Fulfilled የብሉይ ከመዳን የትንቢት ፍጻሜ ነው ። — ማቴዎስ 5፥17 (አዲሱ መ.ት) ። ""ሕግንና የነቢያትን ቃል ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ለመፈጸም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።"

ኢየሱስ የመጣው የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን ለመፈፀም በእዚህም የአባቱኝ ፈቃድ ለመፈፀም ነው ። ለምሳሌ :- የሴቲቱ ዘር ፣ ኢሳያስ 53 ፣ መዝሙር 22 ፣ የነህሱ እባብ ወዘተ ..።

2ኛ, Atonement is Complete የመሥዋዕቱ ፍጻሜ :— በስቅለቱ ዐውደ ምሕረት፣ τετέλεσται የኃጢአት ዕዳ ሙሉ በሙሉ መከፈሉን ያመለክታል። የብሉይ ኪዳን መስዕዋቶች ለሚመጣው ክርስቶስ ጥላ ነበሩ እንጂ አካል አልነበሩም ። — ዕብራውያን 10 (አዲሱ መ.ት) ። ' ሕጉ ወደ ፊት ለሚመጡት መልካም ነገሮች ጥላ ነው እንጂ፣ እውነተኛው አካል አይደለም፤ ስለዚህም በየዓመቱ ዘወትር ያለ ማቋረጥ የሚቀርበው ተደጋጋሚ መሥዋዕት፣ ለአምልኮ የሚቀርቡትን ሰዎች ፍጹም ሊያደርጋቸው ከቶ አይችልም። 2 ፍጹም ሊያደርጋቸው ቢችል ኖሮ፣ መሥዋዕት ማቅረቡን ይተዉት አልነበረምን? ደግሞም ለአምልኮ የሚቀርቡት ሰዎች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ

ስለሚነጹ፣ በኅሊናቸው ኀጢአተኝነት ባልተሰማቸውም ነበር።

3ኛ, New Covenant Established አዲስ ኪዳን ተቋቁሟል ።

የኢየሱስ ሞት በህግ ስራ ላይ የተመሰረተውን ብሉይ ኪዳን ያበቃል እና በጸጋ ላይ የተመሰረተውን አዲስ ኪዳን ይጀምራል ። — ኤርምያስ 31፥31 (አዲሱ መ.ት) ።""ከእስራኤል ቤትና፣ ከይሁዳ ቤት ጋር" ይላል እግዚአብሔር፤ "አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት፣ ጊዜ ይመጣል።"

በመጨረሻው እራት ጊዜ ኢየሱስ የእዚህ ትንቢት ፍፃሜ መስቀሉ እንደሆነ ይጠቁመናል ። — ሉቃስ 22፥20 (አዲሱ መ.ት) ። "እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን አንሥቶ እንዲህ አለ፤ "ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው ደሜ የሚመሠረት አዲስ ኪዳን ነው።"

በጠቅላላው ተፈፀመ የሚለው Theologically እንድንረዳው ካስፈለገ ፦

The work of redemption is completed.

The debt of sin is paid in full.

The power of death and evil is broken.

The way to God is open.

The old has passed; the new has begun

ክርስቶስ በመስቀል ላይ የተፈፀመው ስራ ለእኛ ያስገኘው ውጤት ።

1ኛ, የኃጢአት ስርየትን ለማስገኘት ። 1ኛ ዮሐንስ 2፥2 ። "እርሱም የኀጢአታችን ማስተስረያ ነው!

ማስተሰረያ ማለት ይቅርታ ማስገኛ ማለት ነው ። ነገርግን ጥያቄው ቃሉ የሚያገለግለው የኃጢአትን በደል በመደምሰስ የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚያበርድ ? ወይስ የእግዚአብሔር ቁጣ በሌለበት ሰውን ከኃጢአት በደል ማንፃት ? በሌላ አገላለጽ ዋናው የመስዋቱ ውጤት የሚታየው በእግዚአብሔር አመለካከት ላይ ነው ወይስ በሰው ሁኔታ ላይ?

እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና ለኃጢአት ቅጣት ያስፈልጋል ። ሕግን መጣስ እንዲሁ ትርጉም የለሽ እውነታ አይደለም ፣ ምክንያቱም ኃጢአት በራሱ በእግዚአብሔር ላይ ማመፅን ይወክላል (1ኛ ዮሐንስ 3፡4)። የኃጢአት ልብ እግዚአብሔርን አለማክበር እና እርሱን አለማመስገን ነው (ሮሜ. 1፡21)። ኃጢአት ለእግዚአብሔር ጌትነት ለመገዛት ግልጽ የሆነ እምቢተኝነትን ይወክላል።

የእግዚአብሔር ፍርድ በኖህ የጥፋት ውሃ፣ በብሉይ ኪዳን የአረማውያን ሕዝቦች ፍርድ፣ እና የእስራኤል የኃጢአቷ መፍረዱ ግልጽ ነው። መጥምቁ ዮሐንስ ሰዎች ከሚመጣው የጌታ ፍርድ እንዲሸሹ ያስጠነቅቃል (ማቴ. 3፡1–12)። መጪው ፍርድ ከመምጣቱ በፊት የሰው ልጆች ንስሐ እንዲገቡ ተጠርተዋል (ሐዋ. 2፡14–39፤ 3፡12–26፤ 4፡8–12)።

የእንስሳት መሥዋዕቶች በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ኃጢአት ሲወስዱ፣ እነዚህ መሥዋዕቶች የሰውን ኃጢአት ሙሉ በሙሉ ማስተሰረይ አይችሉም። ለዚያም ኢየሱስ ክርስቶስ በህዝቡ ቦታ በመተካት ወደ ምድር መጥቶ ሞተ፣ የሚገባቸውን ሙሉ ቅጣት በራሱ ላይ ተቀበለ። ክርስቶስ ህዝቡን ተክቷል ማለት የህዝቡ ቅጣት በእሱ ላይ አርፏል ማለት ነው ። ሮሜ ፫፥፳፭ “በደሙም በሆነው እምነት፣ እግዚአብሔር የማስተስረያ መሥዋዕት አድርጎ አቅርቦታል። እግዚአብሔር ክርስቶስን የኃጢአት መስዕዋት አድርጎ አቀረበው ሲል የኢንግሊዘኛው *propitiation* የሚልን ቃል ነው የተጠቀመው ። ኢየሱስ የሞተው የእግዚአብሔርን ቁጣ ለማቀዝቀዝ ወይንም ቁጣውን ለማርካት ማለት ነው ። ይህ አስቀድሞ በምዕራፍ *1:18* ያለውን የሚያመለክት ነው ። — ሮሜ *1*፥*18* (አዲሱ መ.ት) ። “በክፋታቸው እውነትን ዐፍነው በሚይዙ፣ በዐመፃቸውና በክፋታቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቊጣ ከሰማይ ይገለጣል፤” በኃጢአታቸው ምክንያት ሊገለጥባቸው ያለው የእግዚአብሔር ፍርድ በኢየሱስ ላይ መገለጡን የሚያሳይ ነው ።

በብሉይ ኪዳንም ደም የእግዚአብሔርን ቁጣ ያበርዳል ። አሮን እና ፊንሐስ የእግዚአብሔርን ቁጣ ለማብረድ ማስተሰረያ ሲያቀርቡ እናያለን ። ዘሆ *16:46-48* — ዘኍልቁ *16* (አዲሱ መ.ት) ፵፮ ከዚያም ሙሴ አሮንን፣ “ከእግዚአብሔር (ያህዌ) ዘንድ ቊጣ ወጥቶ መቅሠፍት ጀምሮአልና ጥናውን ወስደህ ዕጣን በመጨመር ከመሠዊያው እሳት አድርግበት፤ ፈጥነህም ወደ ማኅበሩ ሄደህ አስተሰርይላቸው” አለው። ፵፯ ስለዚህ አሮን፣ ሙሴ በነገረው መሠረት ወደ ማኅበሩ መካከል ሮጦ ገባ፤ መቅሠፍቱም ቀደም ብሎ በሕዝቡ መካከል መስፋፋት ጀምሮ ነበር፤ ሆኖም አሮን ዕጣኑን ዐጥኖ አስተሰረየላቸው። ፵፰ እርሱም በሕይወት ባሉትና በሞቱት መካከል ቆመ፤ መቅሠፍቱም ተከለከለ።

እንዲሁም እግዚአብሔር ፍርድ ሊያደርግ ሲመጣ እስራኤላውያንን ያለፈው –የፈሰሰውን የእንስሳቱን ደም አይቶ ነው ። ዘጸአት *12*፥*13* (አዲሱ መ.ት) “ደሙም ያላችሁበትን ቤት ለይቶ የሚያሳይ ምልክት ይሆንላችኋል፤ እኔ ደሙን በማይበት ጊዜ እናንተን አልፋለሁ፤ ግብፅን ስቀጣ መቅሠፍቱ አይደርስባችሁም።”

ስለዚህ የኃጢአትን ይቅርታ አገኝን ስንል ከእግዚአብሔር ቁጣ በክርስቶስ ኢየሱስ የመስቀል ላይ ሞት አመለጥን ማለት ነው ። የክርስቶስ መስዕዋታዊ ሞት የኃጢአትን ይቅርታ አስገኘልን ።

፪ኛ, ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት መልሷል ። — ሮሜ ፭፥*10* (አዲሱ መ.ት) ። “የእግዚአብሔር ጠላቶች ሳለን በልጁ ሞት ከእርሱ ጋር ከታረቅን፣ ዕርቅን ካገኘን በኋላ፣ በሕይወቱማ መዳናችን እንዴት የላቀ አይሆንም!”

የእግዚአብሔር ጠላት መሆን እጅግ ከባድ ነው ። እኛ እና አግዚአብሔር ባላንጣዎች ነበርን ። ክርስቶስ ይህንን ጠብ በሞቱ ሻረልን ። ጠብ ተወግዷል ብቻ አይደለም ። ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን ፣ የአባት እና የልጅ ግኑኝነት ተመስርቷል ፣ ቤተሰብ ሆነናል ማለት ነው ።

ኢየሱስ በሞተ ጊዜ የቤተ መቅደሱ መጋረጃው ተቀደደ ። (ቅድስተ ቅዱሳን የሚባለው ስፍራ የእግዚአብሔርን መገኘት የሚወክል ሲሆን የመጋረጃው ትርጉም ወደ እዚህኛው ወደ እግዚአብሔር መገኘት መግባት አትችሉም ነው ። ኢየሱስ በሞተበት ቅጽበት ግን መጋረጃው ለሁለት ተቀደደ (ማቴዎስ ፳፯:፶፩)። ይህ ማለት አሁን ወደ እግዚአብሔር መድረስ ለሚያምኑ ሁሉ ክፍት ነው ። ይህም በካህናት ወይም በመስዋዕት ሳይሆን፣ በኢየሱስ በራሱ በኩል ።

፫ኛ, በጨለማው አለም ላይ እርሱ ድል በማድረጉ ምክንያት እኛም በሰይጣን እና በሞት ላይ ድል እንድናደርግ አደረገን ። — ቆላስይስ ፪፥*15* (አዲሱ መ.ት) ። “የአለቆችንና የባለ ሥልጣናትንም ማዕረግ በመግፈፍ

በመስቀሉ ድል ነሥቶ በአደባባይ እያዞራቸው እንዲታዩ አደረገ።”

መስቀሉ ሽንፈትን ይመስላል ፣ ነገርግን በእርግጥ ድል ነው።

ኢየሱስ ተፈፀመ ሲል ተፈፀመ የሚለውን ነገር በተመለከተ አስቀድሞ እንደሚያውቅ መመልከት እንችላለን ። ድንገት ኢየሱስ ሊያበላ ሊያጠጣ ሊፈውስ በመጣበት አይደለም ተይዞ የተገደለው ። እርሱ የመጣበትን አላማ ያውቀዋል የአባቱን ፈቃድ ለመፈፀም ነው የመጣው ። በመስቀል ላይ ሆኖ እንኳን እናቱን አስቧታል ። በእዚህም እናተና አባትህን አክብር የሚለውን ህግ አልረሳውም ። ህግን በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ እንኳን ፈፅሟል ። ለድነት የሚያስፈልግ ሁሉ ነገር አልቋል ሌላ ምንም የቀረ ነገር የለም ። እኛ ህይወታችን በክርስቶስ ላይ የመሰረትነው አልቋል ብለን እንጂ እፈፅመዋለሁ ብለን አይደለም ። የዘፍጥረትም ታሪክ የሚነግረን ኢሄንን ነው ። እግዚአብሔር ሰውን ከእረፍት ነው ያስጀመረው ።

One word ~ τετέλεσται ~ "It is Finished" and human history changed for eternity.

በወንድም ተካልኝ ኃ/ሚካኤል